የመጀመሪያው

እስላማዊ ጥናቶቼ





ربِّ زدنی علماً

ጌታየ እውቀትን ጨምርልኝ



All right reserved

© የወጣቱ ተልዕኮ
የወጣቱ ተልዕኮ የኦንላይን እትም 2010
ሰሜን ወሎ ወልድያ

ahmedyesuf29@gmail.com
+251927790323
https://youth-mission.com

የወጣቱ ተልዕኮ
አህመድ የሱፍ

Presented by: Youth-Mission

Online Amharic Islamic Books

Publishing.


بسم الله الرحمن الرحيم

የእስልምና ጥናቶች

ለልጆች

በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

የወጣቱ ተልዕኮ በመጎብኘታችሁ እና ይችን መጽሐፍ ዳውንሎድ በማድረጋችሁ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

ይህን ፋይል ስልካችሁ ወይም ኮምፒውተራችሁ ላይ ማስቀመጥ እና ለእራሳችሁ ወይም ለክፍልጓደኞቻችሁ ማተምና ማባዛት ትችላላችሁ፡፡

ጠቃሚ ሆኖ ካገኛችሁት ለሌሎች ሰዎችም በምትችሉት ሁሉ አስተላልፉት፡፡ ማንኛውም አይነት አስተያየትና ጥያቄ ካለችሁ ahmedyesuf29@gmail.com ላይ ፃፉልኝ፡፡

አመሰግናለሁ!

የወጣቱ ተልዕኮ

ማስታወሻ ለወላጆች

የዚህ መጽሐፍ አላማ ለጆቹን እና የኡማውን ልጆች የእስልምናን ትክክለኛ አቂዳ መሰረታዊ ጉዳዮች እንዲረዱ ማስቻል ነው።

ይች መጽሐፍ ድዛይን የተደረገችው ልጆች በራሳቸው ማንበብ እንዲችሉ በማድረግ ነው።

መጽሀፏ ሁሉን አቀፍ ላትሆን ትችላለች። ይሁን እንጅ ከ4-7 አመት እድሜ ላሉ ልጆች ቀላል እና አሳታፊ ደስ የምትል እንደምትሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

ማውጫ

1. ጌታህ ማነው?
2. ነብይህ ማነው?
3. ሃይማኖትህ ምንድ ነው?

ይህ መጽሐፍ የተሳፈው በኡመ አሲያ

መጽሀፍ የተወሰደው ከኢማሙ ኢብን ከሲር (ረሂመሁላህ) አል-ፉሱል ከሚለው መጽገሐፋቸው እና ከሼህ ኡሰይሚን (ረሂመሁላህ) የኡሱሉ ሰላሳ ትንተና ነው።

ጌታህማነው? مَنْ رَبُّكَ؟

رَبِّي اللَّهُ

ጌታየ አላህ ነው። ጌታየ ያ የሚንከባከበኝ ፣ የሚመግበኝ እና ፍጥረቱን በሙሉ የሚንከባከበው የሚመግበው አላህ ነው።

አላህ እኔን እና እናንተን ጨምሮ ሁሉንም ነገር ፈጥሯል።

አላህ ሁሉንም እንስሳቶች ፈጥሯል።

አላህ እፅዋትን እና ተራራዎችን ፈጥሯል።

አላህ ሰማይን ፣ ፀሐይን ፣ ጨረቃን እና እፁብ ድንቅ ከዋክብትን ፈጥሯል።

አላህ ውቅያኖሶችን እና ወንዞችን ፈጥሯል።

አላህ መልአክቶችን እና የማይታየውን ፈጥሯል።

አላህ ሁሉንም ፕላኔቶች እና ሙሉ ፍትረተ አለምን ፈጥሯል።



አልሃምዱሊላህ ረቢል አለሚን

ምስጋና ለአላህ ለአለማት ጌታ

አሏህን የሚመስል ምንም ነገር የለም!

አይናችነን ፣ እጃችነን ፣ ጤናችነን የሰጠን አሏህ ነው። ይህን ማድረግ የሚችል አካል የለም! አሏህን የሚመስል ምንም ነገር የለም።

እናታችነን ፣ አባታችነን ፣ እህቶቻችነን፣ ወንድሞቻችነን አጎቶቻችነን ፣ አያቶቻችነን የሰጠን አሏህ ነው። ያን ማድረግ የሚችል አካል አለ? የለም! አሏህን የሚመስል ምንም ነገር የለም

አሏህ ከሰማይ በላይ ነው። አሏህ ከሁሉም ነገር በላይ ነው። ልክ እንደ አሏህ ከፍ ማለት ሚችል ነገር አለ? የለም! ...

አሏህ አባትም እናትም የለውም። ልጅም የለውም። ልክ እንደዛ ያለ አለ የለም? የለም!.....

ሁልጊዜ የምንሰራውን ነገር ሁሉ አሏህ ያውቀዋል። ከአሏህ ውጭ የምንሰራውን ነገር ሁሉ ሊያውቅ የሚችል አለ? የለም!.....

አሏህ አንድና ብቸኛ ነው። እሱን የሚመስል ምንም ነገር የለም።

سُورَةُ الإِخْلَاصِ



قُلْ هُوَ ٱللَّهُ أَحَدٌ ١

ٱللَّهُ ٱلصَّمَدُ ٢

لَمْ يَلِدْ وَلَمْ يُولَدْ ٣

وَلَمْ يَكُن لَّهُۥ كُفُوًا أَحَدٌۢ ٤

1 በል! እሱ አላህ አንድ ነው።

2 አላህ የሁሉ መጠጊያ ነው።

3 አልወለደም አልተወለደም።

4 ለእሱ አንድም ቢጤ የለውም።

አልተወለደም አልወለደም ማለት ወላጅም ሆነ ልጅ የለውም ማለት ነው።

<u>የማሰቢያ ጊዜ</u>

አላህ ልጆች አሉት እንዴ?

አላህ ሁልጊዜ ምግብ ይሰጠኛል

ዘወትር ከእንቅልፌ ስነቃ አሏህን አብዝቼ ለመገዛት ቁርሴን እበላለሁ። ዘወትር አላህ ምግብ ይሰጠኛል። አልሀምዱ ሊላህ!

ዘወትር እንዳይበርደኝ እና ሰውነቴን ለማሞቅ ልብሶቼን እለብሳለሁ። ልብሶቼን የሰጠኝ አላህ ነው። አልሐምዱ ሊላህ!

ዘወትር እናቴ ስታስተምረኝ ላውቅ እችላለሁ። እናታችነን ፣ አባታችነን ፣ ወንድሞቻችነን እና እህቶቻችነን የሰጠን አላህ ነው፡ ፡ አልሐምዱሊላህ!

ዘወትር ስንጫወት ደስይለናል። አላህ ጤነኛ አድርጎናል። አልሐምዱሊላህ! ዘወትር እግሬን ለመራመድ ፣ እጄን ለመፃፍ እጠቀማለሁ። እጆቻችነን መብልያ ፣ መፃፊያ ፣ መስሪያ እና እግሮቻችነን መራመጃ ያደረገልን አላህ ነው። አይኖቻችንን ማያ እና ጆሮዎቻችን መስሚያ ያደረገልንም አሏህ ነው። ምላሳችነን እና ጥርሶቻችነን ሰጥቶናል።

አሏህን እንወደዋለን! ብዙ የማናያቸውና የምናያቸውን ነገሮች ሁሉ ሰጥጦናልና።

እሱ አረዛቅ (ሰጭው) ነው። الرَّزَّاقُ جَلَّ جَلَالُهُ

አላህ አንድ ነው!

ተውሂደሩቡቢያ

ብቸኛው ጌታ አሏህ ነው።

ብቸኛው ጌታ አሏህ ብቻ መሆኑን እናምናለን።


አሏህ አጋር ጓደኛ ፣ ልጅ ፣ እናት አባት የለውም። የምናየውን ነገር ሁሉ የፈጠረው እሱ ነው። ያለንን ነገር ሁሉ የሰጠን እሱ ነው። አልሐምዱሊላህ! አሏህ የምንሰራውን ነገር ሁሉ ያውቃል፡ ፡ በእወውቀቱ እኛ ጋር ነው።

“አንድም ቅጠል አትረግፍም፤ እሱ የሚያወውቃት ቢሆን እንጅ”

(አል-ቁርአን 6፡59)

<u>የማሰቢያ ጊዜ</u>

አሏህ የፈጠራቸውን ልዩ ነገሮች ፃፍ



ተውሂደል ኡሉሂያ

አምልኮ የሚገባው ለአላህ ብቻ ነው።ሁሉም የአመልኮ ተግባራት መሰራት ያለባቸው ለአላህ ብቻ መሆኑን እናምናለን። ይህ ማለት የምንሰራቸውን መልካም እና በጎ ስራ ሁሉ ለአላህ ብቻ ማድረግ ይኖርብናል።

አላህ መጥፎ ስራዎችን አይወድም። ሆኖም ለአላህ ብቻ ስንል ከመጥፎ ስራዎች እንርቃለን።

መፀለይ እና መለመን ያለብን አላህን ብቻ ነው።እሱ የምንፈለገውን ሁሉ ይሰጠናል። አስታውሱ! አላህ ከእኛ ምንም ነገር አይፈልግም፤ እኛ ግን እንፈልገዋለን።

> “በእርግጥ እኔ አላህ ነኝ። ከእኔ ውጭ
> ሌላ አምላክ የለምና ተገዛኝ። እኔን
> ለማስታወስም ሶላትን ስገድ።”
>
> (አልቁርአን 20፡14)

<u>ማሰቢያ ጊዜ</u>

ዛሬ ለአላህ ብላችሁ ልትሰሯቸው የምትችሉ በጎስራዎችን አስቡና ፃፉ

ተውሂደል አስማኡ ወሲፋት

አላህ እፁብ ድንቅ እንከን የለሽ ስሞችና ባህሪያቶች አሉት። በሁሉም የአላህ ውብ እና እንከን የለሽ ስሞች እና ባህሪያቶች እናምናለን። የአላህ ባህሪያቶች ልክ እንደኛ አለመሆናቸውን እናምናለን። ምክኒያቱም እሱን የሚመስል አንድም ነገር የለምና ነው።

አላህ አሰሚዕ ሁሉን ሰሚ ነው። እኛ እንሰማለን ነገርግን በመላ ፍጥረተ አለሙ ውስጥ ያለውን ሁሉ መስማት አንችልም።

አላህ ሁሉን ሰሚ ነው። ምክኒያቱም የአላህ ስምና ባህሪያቶች ፍፁም እንከን የለሽ ፣ጎዶሎ የለሽ ናቸው። አላህን የሚመስል ምንም ነገር የለም

"እሱን የሚመስል ምንም ነገር የለም፤ እሱ ሁሉን ሰሚ ፣ ሁሉን ተመልካች ነው።"

አሰሚዕ ሁሉን ሰሚ

አልበሲር ሁሉን ተመልካች

<u>የማሰቢያ ጊዜ</u>



የምታውቋቸውን አምስት የአላህ ስምና ባህርያቶች አስታውሳችሁ ፃፉ

2 ነብይህ ማነው?

مَنْ نَبِيُّكَ؟ نَبِيِّي مُحَمَّدٌ

ነብያችን ሙሐመድ ናቸው። አሏህ የላካቸው ለሁሉም ሰው ነው።

ነብዩ ሙሐመድ ብላችሁ ስማቸውን ስታነሱ ወይም ስማቸው ሲነሳ ስትሰሙ ሁሌም ሰለሏሁ አለይሂ ወሰለም (የአሏህ ሰላትና ሰለም በእሳቸው ላይ ይሁን) ማለት ይኖርባችኋል።

ነብዩ ሙሐመድ የኖሩት ከረዥም ጊዜ በፊት ነው።

ሙሉ ስማቸው

ሙሐመድ ኢብን አብዱሏህ ኢብን አብዱል ሙጠሊብ ኢብን ሐሽም ነው። ከቁረይሽ አረቦች ነበሩ።

የተወለዱበት ቀን

ነብዩ ሙሐመድ የተወለዱት በእስልምና ወር ረቢኡል አወል ሰኞ ቀን መካ ውስጥ ነው።



የነብዩን መስጊድ አይታችሁ ታውቃላችሁ?

እናቱቸው

የነብዩ ሙሐመድ የእናታቸ ውስም አሚና ነው።።

አባታቸው

የነብዩ ሙሐመድ አባት ስም አብዱሏህ ነው።።

አስተዳዳጋቸው

ነብዩ ሙሐመድ ያደጉት የቲም ሆነው ነው።። ያሳደጋቸውም አያታቸው ናቸው።። ከዚያም አጎታቸው አቡጧሊብ መልካም እንክብካቤ አደረጉላቸው።። ነብዩ ሙሐመድ ሐሊማ የምትባል ሴት ጡት ጠብተዋል።።

ነብዩ ሙሐመድ ወጣት በሆኑ ጊዜ ልክ እንደሌሎቹ ነብያቶች እረኛ ሆነው ሰርተዋል።። እንዲሁም ከአጎታቸው አቡጧሊብ ጋር በመሆን የንግድ ስራ ሰርተዋል።።




ይህ ምን እንደሚል
ታውቃላችሁ

ቁርአን እና ነብዩ ሙሐመድ

አሏህ ቁርአንን ለነብዩ ሙሐመድ የላከው ተውሂደን እንዲያስተምሩ ነው። መልአኩ ጅብሪል ቁርአንን ያመጣላቸው በመካ አቅራቢያ በሚገኝ የሒራ ዋሻ ውስጥ ነው። ነብይ የሆኑት በ40 አመታቸው ነው።

ቁርአን የአሏህ መጽሐፍ ነው።

ዘወትር ሁልቀን ቁርአን ማንበብ እና ማድመጥ ይኖርብናል። ቁርአን በጣም ውብ ነው። ከቁርአን ብዙ ነገር መማር እንችላለን። ለምሳሌ ልክእንደ አስገራሚ የነብያቶች ታሪኮች




ደግ ነብይ

ነብዩ ሙሐመድ ቁርአንን ይወዱ ነበር። የአሏህ መጽሐፍ ይወዳሉ። ምንም እንኳ ሌሎች ሰዎች በእሳቸው ላይ ክፉ ቢሆኑም እሳቸው ግን በጣም ደግ እና አዛኝ ነበሩ። ልክእንደሳቸው ለመሆን መሞከር ይኖርብናል።

ለእሳቸው አንሰግድም

ነብዩ ሙሐመድ 63 አመታቸው በሆነ ጊዜ መዲና ውስጥ ሞቱ። ነብዩ ሙሐመድን በጣም እንወዳቸዋለን። ነገርግን ለእሳቸው አንሰግድም። እምንሰግደው ለአሏህ ብቻ ነው። አሏህ ሁሌም ህያው ነዋሪ ነው። ሁልጊዜ ፀሎታችንን ይሰማናል። አሏህን የሚመስል አንድም ነገር የለም።



ታስታውሳላችሁ

1 የነብዩ ሙሐመድ እናት እና አባት ስም ማንነው?

2 አያታቸው ከሞቱ በኋላ ነብዩ ሙሐመድ ያሳደጋቸው ማነው?

3 ነብዩ ሙሐመድ በልጅነታቸው የሰሩት ስራ ምንድን ነው?

4 ነብዩ ሙሐመድ የተወለዱ ትየት ነው?

5 የነብዩ ሙሐመድ ሙሉ ስም ማን ነው?


6 ነብዩ ሙሐመድ የተወለዱት ሰኞ ቀን ነው?

7 ነብዩ ሙሐመድ ነብይ የሆኑት በስንት አመት እድሚያቸው ነው?

8 ቁርአን ለነብዩ ሙሐመድ የተላከው ለምድነው?

9 ለነብዩ ሙሐመድ መስገድ እና እሳቸውን መለመን ይቻላል?

ማሻ አሏህ!



3 ሐይማኖትህ ምንድን ነው

ሐይማኖቴ እስልምና ነው። እራስን በተውሂድ ለአላህ ማስገዛት ነው።


አላህ ያገዘኝን ሁሉ እንሰራለን። ምክኒያቱም ሙስሊሞች ነን። ሃይማኖታችን እስልምና ነው።

እስልምና ደግና መልካም ሰዎች እንድንሆን ያስተምረናል።

አላህን እንድንታዘዝ እስልምና አስተምሮናል። በላጩን እሱ ያውቃልና።

እስልምና ሐይማኖቴ በመሆኑ በእርግጥ ተባርኪያለሁ።

እስልምናን ሃይማኖቴ አድርገህ ለመረጥክልኝ ጌታ አላህ ምስጋና ይገባህ።



5ቱ አምስቱ የእስልምና ምሰሶዎች

1 ሸሃዳ መመስከር፡ ከአሏህ ውጭ ሌላ አምላክ አለመኖሩን እና ሙሐመድ የመጨረሻው የአሏህ መልእክተኛ መሆናቸውን መመስከር ነው።።

2 ሶላት በቀን አምስት ጊዜ እንሰግዳለን።።ምክኒያቱም ጌታችነን ማመስገን ማወደስ ስለሚገባን።። አምስቶቹ ሶላቶች ፈጅር ፣ ዙሁር ፣ አስር ፣ መግሪብ ፣ ኢሻ ናቸው።።

3 ዘካ እኛ ሙስሊሞች ነን።። ሆኖም ያለንን ነገር ለድሆች ማካፈል እና እነሱን መንከባከብ ይኖርብናል።።

4 ፆም በየአመቱ በረመዷን ወር ከንጋት ጀምሮ ፀሐይ እስከምትጠልቅበት ጊዜ ድረስ እንፆማለን።። ይህ ማለት ቀን ላይ አንበላም ፣ አንጠጣም ፣ መጥፎ ነገርም አንሰራም ማለት ነው።።

5 ሐጅ ከቻልን አንድ ቀን ወደ መካሂ ደን ሐጅ እናደርጋለን።።

6ቱ የኢማን ምሰሶዎች

1

በአሏህ ማመን

ሙስሊሞች ነን።።

በአሏህ እና ምናለን።።

በአንድ ብቸኛ አምላክ እናምናለን።።

እሱን የሚመስል ምንም ነገር የለም።።

አንድም ነገር አይፈልግም!



<u>የማሰቢያ ጊዜ</u>

አሏህ ከፉጡሮቹ እርዳታ ይፈልጋል እንዴ?

2

በአሏህ መልአክቶች ማመን

ሙስሊሞች ነን። በአሏህ መልአክቶች እናምናለን።



ደግና መልካም ፍጡሮች ናቸው። የተፈጠሩትም ከብርሃን ነው።

የሚያመልኩት አሏህን ብቻ ነው። እሱንም ብቻ ይታዘዛሉ።

<u>የማሰቢያ ጊዜ</u>

ቁርአንን ለነብዩ ይዞላቸው የመጣው ማን እንደሆነ ታስታውሳላችሁ ማነው?

3

በአሏህ መጽሐፍቶች ማመን

ሙስሊም ነን፡፡ በአሏህ መጽሐፍቶች እናምናለን፡፡ ጥሩና መጥፎ የሆነውን ነገር ያስተምረናል፡፡

አሏህን ብቻ መገዛት እንዳለብን ያስተንረናል፡፡




<u>የማሰቢያ ጊዜ</u>

ለነብዩ ሙሐመድ የተገለፀላቸው መጽሐፍ ስም መንድን ነው?

4

በአሏህ መልዕክተኞች ማመን

እኛ ሙስሊሞች ነን፡፡ በሁሉም የአሏህ ነብያቶች እና መልዕክተኞች ከአደም እስከ ሙሐመድ ባሉት ሁሉ ከእሱ የተላኩ ስለመሆናቸው እናምናለን፡ ፡



ለአሏህ ብቻ እንድንሰግድ ፣ እሱን ብቻ እንድንገዛ አስተምረውናል፡፡ ለሰዎችም ደግና መልካም ሰው እንድንሆን አስተምረዋል፡፡

<u>የማሰቢያ ጊዜ</u>

ቁርአንን አሏህ ለነብዩ ሙሐመድ አሏህ ያወረደላቸው ለምንድን ነው?

5

በፍርዱ ቀን ማመን

እኛ ሙስሊሞች ነን፡፡

አንድ ቀን አሏህን እንደምንገናኝ፤

ለፍርድ እሱ ፊት እንደምንቀርብ እናምናለን፡፡

ያ ታላቅ ቀን ነው፡፡

6

በቀደር ማመን

እኛ ሙስሊሞች ነን፡፡

በዚህ ፍትረተ አለም ውስጥ የሆነው እና የሚሆነው ነገር ሁሉ በአሏህ እንከን የለሽ እውቀት እና ጥበብ መሰረት በእሱ ውሳኔ ወይም ድንጋጌ ብለን እናምናለን፡፡



የመጀመሪያ እስልምና ጥናታችሁን አጠናቃችኋል!

ስም_____

ቀን_____

ربِّ زدنی علماً

ጌታየዋ እውቀትን ወምርልኝ!


رَبَّنَا تَقَبَّلْ مِنَّا إِنَّكَ
أَنْتَ السَّمِيعُ العَلِيمُ

ማንኛውም አይነት ሃሳብ አስተያየት ካለዎት በኢሜል አድራሻየ ahmedyesuf29@gmail.com ላይ ሊፅፍልኝ ወይም ደግሞ +251927790323 ላይ ሊደወልልኝ ይችላሉ። የወጣቱ ተልዕኮ ኢስላማዊ መጣጥፍችን ለማግኘት https://youth-mission.com ይጎብኙና መልዕክት ያስቀምጡልን። ጀዛኩሙላህ ኸይረን ከሲረን!